# ይድረስ ለ“ዲያስፖራ”

ምንም እንኳን “ዲያስፖራ” የሚለውን ስያሜ የምጠላና አምርሬም የምቃወም ብሆንም ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን ለማጥፋት ላለፉት አርባ ዓመታት፣ከጫካ ጀምሮ ሌት ተቀን ሲሰራ የኖረው ፣በስልጣን ላይ የተቀመጠው የህወሃት ቡድን ሰሞኑን በዚህ ስም አንድ ቢሮ መክፈቱንና በዚህ ስያሜ ሊስተናገዱ የሚችሉትን ኢትዮጵያውያን እያደነ በመሰብሰብ፣በጥቅም ሰንሰለት አስሮ በውጭ አገር ሰርተው የቋጠሩትን ለመንጠቅ ዕቅድ ማውጣቱን ስሰማ በዚህ ተንኮል ሊጠመዱ የሚችሉት የዋህ ወገኖቼን ለመምከርና ከአደጋው ለማዳን ያለኝ መንገድ ሁኔታውን በጽሁፍ ማቅረቡ ብቻ ስለሆነ በዚሁ ርእስ ስር ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ተገድጃለሁ።

በቅድሚያ ዲያስፖራ የሚለው ስያሜ በውጭ አገር ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ተስማሚ አይደለም፤አጠራሩ በጥንት ጊዜ ከሁለትና ከሶስት ሽህ ዓመት በፊት የአይሁድ እምነት ተከታዮች(ይሁዲዎች) ከመኖሪያ አገራቸው ተነቅለው፣በስደት እንዲኖሩ በመገደዳቸውና አገረቢስ ሆነው ለብዙ ዘመን በመቆየታቸው የተሰጠ ስም ነው።እኛ ኢትዮጵያውያን ግን በውጭ አገር ለመኖር ፈቅደንና ተገደን የወጣን፣አገር እያለን በሰላምና በነጻነት ለመኖር ያልቻልን፣ በአገራችን ውስጥ ከሚኖሩት ዘመድ አዝማድ፣ጓደኛና ጎረቤቶቻችን ጋር በቀጥታና በተዘዋዋሪ ፣አልፎ አልፎም በአካል የምንገናኝ፣ሁኔታም ከፈቀደልን አገራችን ገብተን ለመውጣት ወይም ለመኖር የምንችል ሕዝቦች እንጂ አገር ጠፍቶ አገረቢስ ሆነን ተበታትነን የቀረንና የምንቀር ዜጎች አይደለንም።ጊዜው ሲደርስና አገር ጥለን የወጣንበት ምክንያት ሲወገድ፣የዜጎች መብት የሚከበርበት ስርዓት ሲሰፍን ተመልሰን ልንገባ የምንችል፣የምንኖርበት አገርና ሕዝብ ሳይቀር የመጣንበትን የሚያውቅና በዚያው ዓይን የሚመለከተን፣ኢትዮጵያውያን ነን።የህወሃትና ተባባሪዎቹ ዓላማ ግን አገራችን ድምጥማጧ ጠፍቶና ተበታትና በያለንበት ተበታትነን እንድንቀር፣እንኳንስ በአገርነት ኢትዮጵያ የሚለው ስምና ዜጋ ከምድር ገጽ እንዲጠፉ ማድረግ ነው። ስለሆነም በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ብሎ ከመጥራት ይልቅ ዓላማቸውን በሚያስተናግድ “ዲያስፖራ”በሚል ቅጽል መጥራቱ ይቀላቸዋል።መጥራት ብቻም ሳይሆን በዚሁ ስም የገቢ ምንጭ የሚሆን ጽ/ቤት በይፋ አቋቁሞ ጉባኤ እስከማካሄድ ደርሷል።

ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት በባርነት ከአፍሪካ ተገደው የተወሰዱት ትውልድ የሆነው ጥቁር አሜሪካዊ እንኳን ዲያስፖራ ተብሎ አልተጠራም፤ይባስ ብሎም የመጣበትን አገር ምንጭና ታሪክ ላለመርሳት አፍሪካዊ-አሜሪካዊ (አፍሪካን አሜሪካን) በሚል ስም ለመጠራት ያላሰለሰ ትግል አድርጎ ተሳክቶለት በዚሁ ለመጠራት በቅቷል።እኛ ግን የተጠነሰሰልንን መርዝ ሳንጠራጠር፣ሹመት ወይም ውዳሴ አድርገን በመቁጠር “ዲያአስፖራ” ብለው ሲጠሩን ካለምንም ቅሬታ ተቀብለን አቤት እንላለን።በስማችንም ለተቋቋመው ጽ/ቤት ሽሽግ ዓላማ ሰለባና ለመሪዎቹም የውጭ አገር ምንዛሪ የገቢ ምንጭ ለመሆን በየስብሰባው አዳርሽ ውስጥ ስንራኮት፣ከሕዝብ እየተነጠቀ ለሚሸጥልን መሬትና ቤት ግዥ ስንረባረብ እንገኛለን።እስከአሁን ጊዜ ድረስ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለአገር አጥፊው መንግስት ተባባሪዎች ሆነናል፤ከአሁን በኋላ ግን ቆም ብሎ

ጉዞአችንን መመርመር ያስፈልገናል።ጊዜ ካለፈና ስብራቱ እውን ከሆነ በኋላ መጸጸቱ አይጠቅምም፤ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ እያየን የተፈጸሙትና የፈጸምናቸው ስህተቶች ለወደፊቱ ትምህርት ሊሆኑን ይገባል።

የጽህፈት ቤቱ ዓላማና ስራ በዚሁ “ዲያስፖራ” እያለ የሚጠራውን ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ በውጭ አገር የሚኖር ዜጋ ያለውን አገራዊ ፍቅርና በአገሩ የመኖር ፍላጎት እንደ ደካማ ጎን በመጠቀም ንብረቱን ዘላቂ ዋስትና በሌለው የስራ ዘርፍ ላይ እንዲያውል ብዙ የማታለያ እቅዶችን መዘርጋትና ማታለል ነው።ከነዚህም ውስጥ በአገር ውስጥ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ያላገኘውን፣የቦታ፣የቤትና የብድር መብትና ዕድል በመስጠት ኢትዮጵያን በማፈራረሱ ዘለቄታ ግብ እንዲተባበር የሚያደርገው ዘመቻ ነው።

በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አብዛኛው አገሩን የሚወድ፣አገሩ ተሻሽላና አድጋ ማየት የሚፈልግ፣አምባገነንነት ተወግዶ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍን፣የዜጎች እኩልነት ተከብሮ አንድ ጠንካራ ኢትዮጵያ እንድትኖር፣ የጎሳ ፖለቲካ ተወግዶ ዘመናዊና ሕዝብን ያሳተፈ የፖለቲካ አሰራርና ባህል እንዲኖር ከልብ የሚመኝና ለዚያም የሚታገል ነው።ይህ ማለት ግን በዘርና በጎሳ ልክፍት የተለከፉት ከህወሃት ዓላማ ጋር የሚመሳሰል ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያዊነት አቋም ያላቸው የሉም ማለት አይደለም፤እንዳሉ አይካድም።በነዚህ አይነቶቹ ጸረ ሰላምና ጸረ ኢትዮጵያ አድርባዮች አማካኝነት የስለላና የሽብር ሰንሰለት ከአገርቤት ጀምሮ በውጭ አገራት መዘርጋቱን ሁሉም ስለሚያውቀውና ስለሚረዳው መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም።ግን በዚህ የስለላ መረብ ላለመጠለፍ መጠንቀቅና በስለላው የተሰማሩትን ማሳፈር እንደሚገባ ማሳሰብ ተገቢ ነው።የስለላው መረብ፣በሃይማኖትና በማህበረሰብ ድርጅቶችና ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ሰርጎ ገብቷል።የሚጠቀሙበት ብልሃት አገርን በማልማቱ ስራ መተባበርና አካል መሆን የሚል አገር ወዳዱን ለመሳብ የሚችል ግን ባዶ መፈክር በመንዛት ነው።

አገር ለመገንባትና ለማሻሻል ገንዘብ ብቻ በቂ አይደለም፣ዕውቀት፣ቀና አስተሳሰብ፣ዴሞክራቲክ አመለካከት፣የተሻለ የፖለቲካ አሰላለፍና አሰራር፣አገር ወዳድነትን፣ጠባብነትን መቃወምና ማሶገድ፣ጉቦና ሙስናን ማጥፋትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።እነዚህ ከገንዘብና ከነጻነት ጋር ሲዋቀሩ አገር ያድጋል፣ ይለማል፣የሕዝብ ኑሮ ይሻሻላል።ያ በሌለበት፣ጥላቻ፣ጎሰኝነትና አምባገነንነት በሰፈነበት አገር የገንዘብ ተራራ ቢፈስ ሕዝብን የሚያረካ ለውጥ አይመጣም፤አገርም አደገ፣ለማ ለማለት በቂ አይሆንም።የአብዛኛውም ኢትዮጵያዊ ፍላጎትና ምኞት በዚህ መስክ ውስጥ ተሰልፎ የየችሎታውን ማበርከት ነው።የንግድና የንብረት ማካበት ፍላጎትማ ከሆነ የግዴታ ኢትዮጵያ መሄድ አያስፈልግም፤ በሌሎቹ የአፍሪካ አገሮችም ሆነ በአውሮፓና አሜሪካ እጅን ዘርግቶ የሚቀበል ፣ከበርቴዎችን የሚንከባከብና ዋስትና የሚሰጥ ስርዓት አለ።

በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ገና ከጥዋቱ የኢትዮጵያውያኑን ሁለገብ ተሳትፎ በሕገ መንግስቱ ገድቦታል።ገንዘባቸውን አፍሰው በኤኮኖሚው ዘርፍ እንዲሳተፉ እንጂ በወሳኝ በሆነው የአገር ጉዳይ፣የሰብአዊ መብትና የፖለቲካ ጥያቄ ላይ ትችትም ሆነ ሃሳብ

እንዳያቀርቡ በጥብቅ ይከለክላል።በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍም ሆነ መደገፍና መንቀፍ እንዲሁም መምረጥና መመረጥ ጭራሽ የተከለከለ ነው።ታዲያ አንድ ኢትዮጵያዊ በተወለደበት አገር ጉዳይ ላይ ድምጹን ካላሰማ፣ካልተሳተፈ ከውጭ አገር ባለሃብቶች በምን ይለያል? የኤኮኖሚው ፖሊሲና እንቅስቃሴ እኮ ከአጠቃላዩ የፖለቲካ ፖሊሲ ተነጥሎ አይታይም።ሁሉም ዘርፍ የሚነደፈው ከፖለቲካው መስመር አንጻር ነው።የሚገርመው ነገር የውጭ አገር ከበርቴዎችና ተወካዮቻቸው የመንግስት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አማካሪና ተባባሪዎች መሆናቸው እየታወቀ ኢትዮጵያውያኑን ሚና ቢስ ለማድረግ ሕግና ደንብ መጽደቁ ነው።

በዲያስፖራ ስም የተቋቋመው ጽ/ቤት የሚያካሂደውን ስራ የጽ/ቤቱ ሃላፊ የሆኑት አቶ ፋይዛል አልዩ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጭ  ሲገልጹ የገንዘብ ፈሰሳ እንጂ የፖለቲካም ሆነ ኢትዮጵያዊነትን የሚያንጸባርቅ ተግባር ላይ ለመሰማራት እንደማይፈቀድለት በግልጽ ተናግረዋል። በሳቸው አባባል ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ የሚያምን በውጭ አገር የሚኖር ዜጋ ሊሰራና ሊኖር የሚችለው በተወለደበት ጎሳ ክልል ውስጥ ብቻ ነው።ማለትም የትግሬ ተወላጅ ወደ ትግሬ፣የኦሮሞ ተወላጅ ወደ ኦሮሞ፣የአማራውም ተወላጅ ወደአማራ ክልል በመሄድ ከክልሉ አስተዳደር ጋር በመረዳዳት ሊኖርና ሊሰራ እንደሚችል ተናግረዋል። ይህ ማለት ኢትዮጵያዊ ነኝና በመረጥኩት የኢትዮጵያ መሬት ለመኖርና ለመስራት እፈልጋለሁ ቢል እንደማይሳካለትና እንደማይፈቀድለት በግልጽ ቋንቋ ተናግረዋል።ሙሉ ቃለ መጠይቁን በሚከተለው ሊንክ ማዳመጥ ይቻላል።

Interview with Feyisel Alysi ,published on 28th august 2015 by ato kassahun Negewo

http://www.sbs.com.au/yourlanguage/amharic/en/content/interview-feyisel-alyi

በውጭ አገር የምትኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ “ዲያስፖራ” የሚለውን አጠራር አትቀበል!!

የኑሮ ግዴታ ሆኖብህ ወጣህ እንጂ አገር አጥተህ አይደለም።ያችን ጥለሃት የወጣሃትንና የምትወዳትን ሁኔታም ሲፈቅድልህ ተመልሰህ ልትኖርባት የምትችልባትን አገርህን ለመበታተን፣ስምህንና ማንነትህን እየነፈጉህ መሆኑን እወቅ!!

ህልውናህን ለማሳጣት እንደሚጥሩ ሁሉ ለፍተህ፣ጥረህና ግረህ ያፈራኸውን ገንዘብ በተጭበረበረ ዘዴ ሊነጥቁህ እንደተነሱ ተገንዘብ!! ባለፉት ዓመታት አገራቸው ገብተው ለመስራት ወስነው ንብረታቸውን ተነጥቀው የተመለሱትን ኢትዮጵያውያን ጠይቅ!!ችግር የደረሰባችሁም ለወገኖቻችሁ አስረዱ!! ወገኖቻችሁን እናንተን ከገጠማችሁ የመንግስት ዘረፋ አድኗቸው!!!

በአገር ውስጥ የሚኖረው በሚሊዮን የሚቆጠር ወገንህ እየተፈናቀለ ቤት አልባ፣ስራ አጥ ሆኖና መብቱን ተገፎ በስቃይ በሚኖርባት አገር አንተ ደስተኛ ሆነህ ለመኖር እንደማትችል፣ብትችልም ለአጭር ጊዜ እንደሆነ ተረዳ!!

በሰላም ሰርተህ ልትኖር የምትችልባት አንድነቷን የጠበቀች አገር እንድትኖርና ለእውነተኛ ለውጥ፣ዋስትና ላለው ኑሮ የሚያበቃ ስርዓት መስፈን የሚቻልህን ሁሉ አድርግ።ተመሳሳይ ፍላጎትና ዓላማ ካላቸው ጋር አብረህ ተሰለፍ፤ተባበርም!!!

የሚያስተማምን ስርዓት ሲሰፍን የምታደርገው ተሳትፎ የተሳካና ዋስትና ያለው የሚደገፍና የሚያስመሰግንህ ይሆናል።በአሁኑ ስርዓት ስር ግን የድካምህ ውጤት ክስረትና ብስጭት ሆኖ ይቀራል።

በውጭ አገር የሚኖረው ኢትዮጵያዊ እንጂ "ዲያስፖራ" አይደለም!!ስለሆነም መጠሪያ ቃሉን አትቀበል!!

የተዘረጋው ወጥመድ ይከሽፋል!!

አገሬ አዲስ